# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 4 ቁጥር 4 — መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፲፪ ዓ.ም.


## ዐባይ ለኢትዮጵያችን

*የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ* (https://www.youtube.com/watch?v=rk8118gl21U )

በቅድሚያ እጅግ በአሳሳቢ ሁኔታ በመዛመት ላይ ላለው ኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ "እግዚዮ" የምንልበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ይህ ሁኔታ በአጠቃላይ በዓለም ደረጃ ስለ እራሳችን ስናወራ በሀገር ደረጃ አሳዛኝና አስከፊ ዘግናኝ ጉዳት እንዳያደርስብን "አቤቱ ይቅር በለን፣ ምህረትህ አይለን፣ አጢያታችንን አስተጸርይልን" እያልን አምላካችንን እንለምናለን። ፈጣሪ ምህረቱንና ቸርነቱን ይስጠን። አሜን!!!

የወቅቱ የሀገራችን ፖለቲካ ወደ ብሔራዊ አጀንዳ የመቀየር አዝማሚያ ቢያሳይም የዘረኝነት ጉዞውም አልተለወጠም። አዎ! ሀገር ስትወረር፣ ዳር ድንበሯ ሲደፈር ዘር ሃይማኖት ሳይለዩ ቀደምት አባቶቻችን እነሱ ሙተው ሀገር አኑረዋል። ስለ ቅኝ አገዛዝ ታሪክ ሲወራ የእነሱ ጀግንነት ኮ…ራ! እንድንል አድርጎናል። ዐድዋ ሲነሳ ወኔአችን ይግላል፣ ስሜታችን ዘራፍ ይላል። ጀግኖቻችን ዳር ድንበሯን አስከብረው ያቆዩአት ሀገራችንን ድንበር እየጣሰ፣ አፈር እያጋዘ፣ ግንድ እየተሸከመ "እስከመቼ?" ያሰኘን አካላችን "አንድ ቀን" እያልን ስንጠብቀው ዛሬ ብሔራዊ መነጋገሪያ ይሆን ዘንድ ብቅ ብሏል። ለዘመናት ውስጣችንን ያቆሰለው፣ ከዘፈንና ከንጉርጉሮ ያልዘለለው ይህ ዱር አዳሪ "መቼ ለኢትዮጵያ ሊቆም? መቼ ሕዝብ ሊመግብ?" ጥያቄያችን ለአንዴም ለመጨረሻም መልስ ማግኘት እሚገባው ወቅት ላይ ደርሰናል። "ኢትዮጵያዊነት ለዐባይ፣ ዐባይ ለኢትዮጵያችን" የምንልበት ጊዜው አሁን ነው።

ዐባይ ኢትዮጵያ ነው። ዐባይ ቋንቋው፣ ዘሩ፣ ሃይማኖቱ፣ ሀገሩ፣ ክልሉ ኢትዮጵያ ነው። ድህነትና ብልሹ አገዛዝ "ዐባይ ወጥቶ አዳሪ" አስብሎታል። የዐባይ ውሃ የሀገራችንን ደለል አፈር እየተሸከመ ያለአንዳች ቀረጥና ክፍያ ለግብጽ ሲያሻግር ኖሯል። ኢትዮጵያ ሀብቶቿን ትመለከት ዘንድ መሪ አላገኘችምና ዐባይ ሃይ! ባይ አጥቶ ሲጋልብ ኖሯል። ዐባይ በኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ እንዳያገለግል በድህነት ላይ ሥልጣን ወዳድ አገዛዞች ስደተኛ አድርገውታል። ኢትዮጵያ ተፈጥሮአዊ ውበቷን፣ ደንና ዱር አራዊቶቿን፣ ወንዞቿን፣ ስምጥ ሸለቆዋን፣ ተራሮቿን፣ በቅጡ አልተመለከተችም። ተከዜ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ኦሞ፣ ገናሌ ሌሎች ወንዞቻችን ሲንከራተቱ ውለው ቢያድሩ፣ ከተራራ ቢላተሙ፣ ቢዘሉ፣ እያጓሩ ቢምዘገዘጉ ተመልካች፣ አድማጭ አላገኙም። እስከ ድህነቷ የምንወዳትን ሀገራችንን ጠብቀው ላስረከቡን አባቶቻችን፣ እናቶቻችን ከምስጋና አልፎ አርኣያ ልንሆን የምንችለው ዐባይን የሀገር ሲሳይ ስናደርግ ነው። ***ዐባይ መብታችን ነው። ዐባይ ግዛታችን ነው። ዐባይ ዘራችን ነው። ዐባይ ሰንደቃችን፣ ዐባይ ሕይወታችን፣ ዐባይ ኢትዮጵያችን!!!***

አንድ መንግሥት ሕዝባዊ ሆነ አልሆነ፣ ዴሞክራቲክ ሆነ አልሆነ በሀገራችን ሉዓላዊነት፣ በዳር ድንበሯ ክብር የሚነሱ ብሔራዊ አጀንዳዎች የሕዝብ ናቸውና ሕዝብ ዋናውን ሚና ይጫወታል።

*ማንም መንግሥት ያንሳው ዐባይና ኢትዮጵያ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። ምንሊክ ". . . ያገሬ ሰው እስከዛሬ ያስቀየምኩህ አይመስለኝም . . ." ብለው "ክተት" ሲሉ ቂሙን ወርውሮ ሀገር ተከትሏቸዋል፣ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ". . . ተነስ! . . ." ሲል ወረራ ነውና ሀገር ተነቃንቋል፣ ወያኔ ". . . ባድመን. . ." ሲል ድንበር ነውና በሺዎች ረግፈዋል። ምኒልክ ". . . ማርያምን ትጣላኛለህ. . ." ሲሉ "ደሞ ለሳቸው" ብሎ ያፈገፈገ ከቶም አልነበረም፣ መንግሥቱ ". . . ሱማሌ ወራናለች. . ." ሲል "ደሞ ለገዳይ" ብሎ ጀርባውን የሰጠ አልነበረም፣ ወያኔ ". . . ሻቢያ. . ." ሲል ". . . ደሞ ለገንጣይ፣ አስገንጣይ. . ." ሳይል "እሽው!" ያለው ወጣት ነው ኢትዮጵያዊነቱን ያሳየው፣ ደሙን ያፈሰሰው። በመለስ ዜናዊ የተጀመረውና ዛሬ በዶክተር ዐብይ እየተጠናከረ የመጣው የዐባይ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የኢትዮጵያችን የህልውና ጉዳይ መሆኑ አጠያያቂ ሊሆን አይገባውም። "እንደው ብቀጥን. . ." እንዳለችው እንደው ብንደኸይ፣ እንደው ብንናከስ፣ እንደው ዘረኝነት ቢጦዝ ዐባይ አንድነታችን፣ ዐባይ ፍቅራችን፣ ዐባይ ክብራችን መሆኑን ለአንዴም ለመጨረሻ እልባት የምንሰጥበት ሀገራዊና ብሔራዊ አጀንዳ ላይ ደርሰናል።*

*የዐባይ ድንበር አቋራጭ ጉዞ አፈራችንን አራግፎ፣ ሕዝባችንን መግቦ፣ ኢትዮጵያን አብርቶ መሆን ይኖርበታል። <u>**የዐባይ ማደሪያ ህዳሴው ግድብ የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ አጀንዳ መሆን ይገባዋል።**</u> ዐባይ የሀገር፣ የሕዝብ አጀንዳ መሆን ይገባዋል። ዐባይን ለፖለቲካ ጠቀሜታ ለማዋል የሚደረገው ጉዞ መቆም ይገባዋል። ዐባይ የኢትዮጵያ ህልውና ነውና!*

*ኢትዮጵያችን ዐባይን የመጠቀም ጉዳይ ከጥያቄ ሊገባ አይገባውም። ከአለፉ ታሪኮች መማር እየተሳነን እንጂ በሀገራችን የባዕዳንና የውጭ ኃይሎች ተደጋጋሚ ጥቃት የዛሬ አይደለም። ጣልያን፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ሀገራችንን ለመቀራመት ብቻ ሳይሆን እርስ በእርሳችንም እንናቆር ዘንድ መሠሪ ተግባራቸውን፣ መርዛቸውን የረጩብን ጥንት ነው። የውጫሌው ውል መሠሪ አንቀጻቸው ነው የዐድዋን ጦርነት የቀሰቀሰው። ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር በእምዬ ምንሊክ መሪነት ነፃ የወጣችው ሀገራችን የዓለም ሀገራት ደንብና ሕግ ተጥሶ በ1928 ዓ.ም. (እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1935) ዳግም በኢጣልያ ስትወረር ለወራሪው ኃይል ድጋፍ የሰጡና ያሾፉብን መንግስታት ቀላል እንዳልነበሩ ታሪክ ይነግረናል። ቀደም ሲል በዓፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ክፍያ የተደረገባቸውን የጦር መሣሪያዎች (ታንኮች) ወታደራዊው መንግሥት ላይ ባለው ጥርጣሬ ምክንያት ለኢትዮጵያ እንዳይሰጡ የከለከለው የአሜሪካ መንግሥት የካርተር አስተዳደር ነበር። በ1983ቱ ደርግ፣ ወያኔ፣ ሻቢያና ኦነግን አካቶ ሊካሄድ የነበረውን የለንደኑን ጉባኤ በአደራዳሪነት መጥታ ወያኔን "አዲስ አበባ ግባ!" ብላ ትዕዛዝ የሰጠች አሜሪካ ዛሬም ግድቡ እንዳይሞላ ትዕዛዝ ሰጥታናለች። ከታሪክ መማር ያቃተን፣ የሚደረግብን እና የተደረገብንን ጥቃት እየዘነጋን መልሰን የምናሸረግድላቸው እራሳችን ሆንና ተቸገርን እንጂ አሜሪካ ስለ ኢትዮጵያ ቀና አስባም አታውቅ። ይህ ደግሞ የተመረጡት ፕሬዘዳንቶች አቋም ሳይሆን በፖሊሲ ደረጃ ያለ በመሆኑ ኢትዮጵያ ዕድገትና ብልጽግና ካሳየች አፍሪካን ታሳጣናለች የሚል ስጋት ስላላቸው በተንኮል መረባቸው ያጠምዱናል። ስለ ድህነትና ጦርነታችን የሚያራግበው ሲኤን ኤን ስለ ምርጫ 1997 ዓ.ም. እንቅስቃሴና እልቂት ዘግቦን ያውቃልን? በዘመነ መለስ አገዛዝ በተለይ በዋሽንግተን ዲሲ የሚካሄደውን አቤቱታና ሰልፍ እንደዜና በሲኤን ኤን ተዘግቦ ያውቃልን? ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል ደስታዋን በጭፈራ ያሳየች ሔርኒ ኪሊንተን አልነበረችን? በዘመነ ኦባማ ምርጫ ዳር እስከዳር የተደገፈው ኦባማ መለስ ዜናዊን "ዴሞክራት መሪ" ብሎ ሲያሾፍብን ምን እየነገረን እንደነበር ተገንዝበናልን? "ሆድ ሲያውቅ. . ." እንዲሉ አምባገነን፣ ፋሽስት፣ ዘረኛ፣ ገንጣይ አገዛዞች ምክንያት ዜጎቻችን ለእንግልት፣ ለድህነት፣ ለስደት ተዳርገና "ማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ" አይሁንና ጉዳዩ እውን አሜሪካ ለኢትዮጵያ ቀና ናትን? አሁንም በዐባይ ጉዳይ ላይ የሰጠችው ትዕዛዝ በሀገራችን ጉዳይ በተደጋጋሚ ከምትፈጽማቸው ታሪካዊ*

ስህተቶች ለይተን ማየት አይገባንም። አሜሪካ ብዙ የውሃ በተለይ ዐባይ ላይ በፖይንት ፎር በሚባለው ድርጅት በኩል ጥናቶችን ሠርተውልናል፣ በውትድርናም በተለይ አየር ሃይልን በማሰልጠን፤ በፒስ ኮርፕስ አስተማሪና በጎ አድራጎት ሠራተኞችን ልከውልናል፣ በድርቅና ረሃብ ጊዜም ደርሰውልናል። ያው በራሳቸው የተፅዕኖ ክልል ዕቅፍ ውስጥ ለማስገባት ቢሆንም በተለይ በቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ከአሜሪካ ጋር ከመቶ ዓመት በላይ የቆየ ዲፕሎማቲክ ግንኙነት ነበረን፤ ብዙ ስደተኞችንም አስጠግታልናለች ይህም ሆኖ ግና የአሜሪካን መንግሥት ላለፉት 40 ዓመታት ያህል የኢትዮጵያችንን ብሔራዊ ጥቅምና ሉዓላዊነትን የሚፃረሩ ፖሊሲዎችን አስፈፅማለች ማለት ይቻላል።

በሌላም በኩል የአረቡ ዓለም ኢትዮጵያ ላይ በየጊዜው የሚያደርጉት ጥቃት ነጋሪ አያስፈልገንም። ጥንት ከመሀዲስት ወረራ፣ ከቱርኮች ሤራ፣ ከየመን ተንኮል በአጠቃላይ የአረብ ሀገራት ኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሲሰነዝሩ ለመኖራቸው ማንም ኢትዮጵያዊ ጠንቅቆ የሚያውቀው ነው። ለአለፉት 27 ዓመታት ሀገር በህወሓት/ኢሕአዴግ እየታመሰች ኑሮና ብልሃቱ ለኢትዮጵያ ልጆች ገደል እየሆነ ሲመጣ ሰይጣናዊ አማራጭ እንዲሉ በአረቡ ዓለም ለስደት የተዳረጉ እህቶቻችንን ስንቱን አሰቃይተዋል፣ በአሲድ ጠብሰዋል፣ ገድለው ቀብረዋል። የታረዱ ወንድሞቻችንስ እውን እረሳናቸው??? ሀገራችን ገብተው ማድረግ ያልቻሉትን እየሄድን ታረድንላቸው፣ ተቃጠልንላቸው፣ ከፎቅ ተወረወርን፤ ይህ ነው ተግባራቸው። በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ነጻ አውጭነን ያሉ ድርጅቶችን ከበስተጀርባ አረቡ ዓለም በገንዘብ፣ በመሣሪያ፣ በስልጠና ያልረዳው የፖለቲካ ድርጅት "እስቲ እኔ ነኝ ይበል?"

በ27 ዓመቱ የዘረኛው ኢሕአዴግ አገዛዝ የሀገራችን በር ወለል ብሎ ተከፍቶላቸው ሀገራችን ላይ እየተደረገ ያለው "ታላቁ ሤራ" አሁንም ያላባራና ለሀገራችን እልውና በአሳሳቢ ደረጃ እየተገፋና እየተጠናከረ መሆኑ የአደባባይ ሚስጢር ነው። በቅርቡ በፌደራሉ የወንጀል መከላከል በቁጥጥር ሥር የዋለው ሁለት ኮንቴይነር መሣሪያ (ወደ 18 ሺህ የሚጠጋ ሽጉጥ) መያዝ የሚያመላክተው ይህ ሲገባ የመጀመሪያው እንዳለመሆኑ የመጨረሻውም እንደማይሆን ነው። መንግሥት ባለበት ሀገር ከቱርክ አዲስ አበባ ገብቶ ሲከፋፈል ምን ያህል የመንግሥት አካላት ሁሉ እንደሚሳተፉ መገመት አዳጋች አይደለም። ይህ ሁሉ ትንታኔ አረብ ሊግ በዐባይ ጉዳይ ከግብጽ ቢወግኑ ሊደንቀንም፣ ሊገርመን አይገባም።

በጥቅሉ ኢትዮጵያችን ለበርካታ ዓመታት እልባት ያላገኘውን የዐባይ ጉዳይ የመብትና ነፃነት ጥያቄ ነውና እልባት ልትሰጠው ይገባል። ***<u>የህዳሴው ግድብ ብቻ ሳይሆን ዐባይም የእኛ ነው ለማለት መድፈር ይኖርብናል።</u>*** ለዚህ ደግሞ ሕዝባችን በዐባይ ጉዳይ ከርቀት ሳይሆን ዐባይ ገስግሶ ምላሽ እንደሚሰጥ ልንጠራጠር አይገባምና "ዐባይ ለኢትዮጵያችን!" ይሁን መፈክራችን። የሁኔታውን አሳሳቢነት በመገንዘብ መደረግና መወሰድ ያለባቸውን አንዳንድ ነጥቦች ቀጥለን እናስቀምጣለን፦

1) ከመንግሥት ወገንተኝነትም ሆነ የብሔር ፖለቲካ የፀዳ

ይህ የዐባይ ግድብ ብሔራዊ ጉዳይ ነው፤ በመሆኑም የመንግሥት ፍላጎት ወይም የፓርቲና ብሔር ፖለቲካ ወይም ሌላ ፍላጎት በዚህ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ተፅዕኖም ሆነ ሚናም ሊኖረው አይገባም። መንግሥት ሊከተለው የሚገባው አካሄድ የመላ ኢትዮጵያን የረጅም ጊዜ ብሔራዊ ጥቅምና ሉዓላዊነተን በሚያስጠብቅ መንገድ እንጂ ለአጭር ጊዜ ድጋፍ ወይም የውጪ ተፅዕኖን ሰበብ በማድረግ ለብዙ ዓመታት ጉዳት የሚያስከትሉ ውሎችን መፈራርም አይደለም። ግብፅ ከመቶ ዓመት በላይ ያስቆጠሩ የቅኝ ግዛት ዘመን ውሎችን የምትጠቅሰው ጥቅሟን ስለሚያስጠብቁላት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም የቀድሞም ይሁን አሁንም የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችና

ስብስቦች የግድቡ ጉዳይ የእነርሱ ብቻ እንደሆነ ወይም በእነርሱ መሪነት የሚፈፀም አድርጎ በመቁጠር ከማንኛውም አግላይነት ሊቆጠቡ ይገባል። ግለሰቦችም እንደዛው። በተጨማሪም የዘውግ ፖለቲካ ደጋፊዎች በአንድ በኩል የዐባይ ግድብ ጉዳዩ የማይመለከታቸው አድርገው የሚቆጥሩ በሌላ በኩል ደግሞ "የእኛ ብቻ ነው" የሚሉ አመለካከቶች ይደመጣሉ። ይህ ሀገራዊ አንድነትን የሚከፋፍል ጎጂ እሳቤ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩን እጅግ አጥብቦ ማየትና ሊሰጠው የሚገባውን ትኩረት ማቃለል ነው።

ይህን ሀገራዊ ጉዳይ በተመለከተ የግብፅ መንግሥት፣ ሕዝብ፣ ፖለቲካ ቡድኖች ወዘተ ያላቸውን አንድነትና ቁርጠኝነት ማስተዋል ለሁላችንም ትምህርት ሊሆን ይገባዋል። ሀገራችን ኢትዮጵያን በዘርና ቋንቋ የመከፋፈሉ ውጤት አንድነታችንን አሳጥቶ "ከሞኝ ደጃፍ. . ." እንዲሉ "ጊዜው አሁን ነው" ያለችው ግብጽ ዐባይን "ነቅላ ለመውሰድ" የተያያዘችውን ዘመቻ መቋቋም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ በዐባይ ጉዳይ ለአንዴም ለመጨረሻ ህልውናዋን ያስጠበቀ መብቷን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባታል። ለሀገራዊ አንድነትም ትምህርት የሚያስፈልግበት ጊዜ ላይ ስላለን፤ "የዐባይን ልጅ ውሃ ጠማው" እንዲሉ ነፃነታችንን አስከብሮ የቆየው አንድነታችን ፈተና ውስጥ ገብቷልና ጊዜ እየጠበቀ የሚያገረሸውን የግብጽ ጉዳይ እልባት ለመስጠት ከእነሱ በልጠን የመገኘት ችሎታውም አቅሙም አለንና ይህን ብሔራዊ አጀንዳ ለሕዝባችን ክፍትና ግልጽ አድርገን መወጣት ይኖርብናል።

2) ታሪካዊ አመጣጡና የኢትዮጵያ ሚና

ግብፅ ከጥንት ጀምሮ ዐባይን የራሷ የግል ስጦታ አድርጋ ከመመልከት በላይ፤ የፍሰቱ መጀመሪያ ምንጭ በግዝቷ ስላልሆነ ስጋት ነበራት። ከጊዜ ወደጊዜ ይህ እያደገ መጥቶ፤ በግል ስጦታነት/ንብረትነት ለማቆየት/ለመያዝ ያላት ዕቅድ ለምንም ለማንም የማይመለስ ሆኗል። ይህንን ለማሳካትም የጥቁር ዐባይ ምንጭ ኢትዮጵያችን ስለሆነች ሀገራችን ላይ ዘርፈ ብዙ ሸቀባዎች፣ ሤራዎች አድርጋለች፣ እያደረገችም ነው።

በተለያዩ ነገሥታት ዘመን ቀጥታ ወረራዎች አድርጋለች። ከኦቶማን ቱርክ በኋላም ከእንግሊዝ ቅኝ ገዢዎች ጋር በመተጋገዝና በመመሳጠር የሀገራችንን ወንዝ ከምንጩ ለመቆጣጠር ሞክራለች። ለምሳሌ በአሁን ጊዜ እንኳን ኢትዮጵያችን ያልተሳተፈችባቸውን፣ የልፈረመቻቸውን፣ በቅኝ ግዛት ዘመን የተደረጉ ውሎችንም እንድትቀበል ተፅዕኖ ታደርጋለች።

በተለይ እጅግ የሚያበሳጨውና የአደባባይ ምሥጢር የሆነው በርካታ በኢትዮጵያችን ውስጥ የሚንቀሳቀሱ አማፂ ኀይሎችን በመሣሪያ፣ በመጠለያ፣ በሬዲዮ ሥርጭት፣ በገንዘብና በተለያዩ ሁኔታዎች ድጋፍ ስታደርግ ነበር አሁንም ታደርጋለች። ይህን ለማድረጓ ምክንያቱም ብዙ አያመራምርም፤ ከዚህም አልፎ በዓለም የገንዘብ ተቋማት ኢትዮጵያችን ዐባይ ላይ ለምታቅደው ማንኛውም የልማት ሥራ ድጋፍ እንዳታገኝ አስከልክላለች። ይህም በምታደርገው ጠንካራ ዲፕሎማሲ የታገዘ ነው።

ይህ ሁሉ የግብፅ ረጅም የተንኮል እጅ ወደ ኢትዮጵያ የተዘረጋው ሰላምና ልማት ያላት ኢትዮጵያ እንደጠላት የሚያይ ሁለገብ የማተራምስ ተግባር ነው። እንደ ፈርዖን ዘመን አሥር መቅሰፍት የሚያወርድ ዘመን ላይ ስለሆንን በራስችን አንድነትና ጥንካሬ ይህንን የግብፅ ተንኮል በአንድነት ማስቆም መቻል አለብን።

3) ሰፋ ያለ የዲፕሎማሲና ጉትጎታ (lobbing) ሥራ

ከሰሞኑ ዜናዎች እንደሚታየው ኢትዮጵያችን ቢዘገይም የዐባይን ግድብ በተመለከተ የኢትዮጵያችንን አቋም ለማስገንዘብ ዲፕሎማቶችን ወደ አፍሪካና አውሮፓ ሀገራት ልካለች፤ በጣም ጥሩ ጅምር ነው። አሁን ያለው የኮረና ቫይረስ ስርጭት እንቅፋት ካልሆነ ወደ አሜሪካም ልዑካን እንደሚጓዙ ተነግሯል፡፡ ለማሳሰብ የምንወደው የአፍሪካ ዐባይ ተፋሰስ ሀገራትን ብቻ ሳይሆን ወደ መላው የአፍሪካ ሀገራት ማስረዳትም ይገባል። እንዲሁ ደቡብና ማዕከላዊ አሜሪካ ሀገራትም፤ የእስያ ሀገራትንም ማጠቃለሉ ተገቢ ነው። ጠቅላላ ጉዳዩ ወይም የተወሰነው ክፍል ለግልግልም፣ ለውሳኔም ወደተባበሩት መንግሥታት ሊቀርብ ይችላልና፤ ኢትዮጵያችን በዚህ በዐባይ ጉዳይ የሚቻላትን ያህል ወዳጅና የልማት ሃሳቧን የሚደግፉ ባይሆን ገለተኛ የሆኑ ሀገራት በጣም ያስፈልጓታል እንላለን።

በዓለም አቀፍ ተቋማት እንደ አውሮፓ ሕብረት፤ የእስያ፤ የደቡብ አሜሪካ ሀገራት ሕብረት ወዘተ. ዘንድም የዲፕሎማሲ ሥራ መተግበር ይገባዋል። ከዚህም ጋር የዲፕሎማቲክ ልዑክ ቡድኑ አባላት በችሎታና በአገልግሎት ዘመን ቢመረጡ ተልዕኮው ውጤታማ ይሆናል። በተለይ በአውሮፓና አሜሪካ እንደሚታወቀው መልዕክቱ ብቻ ሳይሆን መልዕክተኛውና ሃሳቡን በተገቢ ሁኔታ አብራርቶ ማቅረቡ ስኬታማነቱን ከፍ ያደርገዋል። አለመታድል ሆኖ ኢትዮጵያችን የብዙ ስደተኛ ዜጎች እናት ነች፤ ነገር ግን እነዚህ በውጪ ሀገራት ያሉ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበትን ሀገር ባህል፤ ቋንቋና ፖለቲካ የሚያውቁና የሚሳተፉትን፤ በአካዳሚክ ምርምር፣ ትምህርት፣ በሕግና ፖለቲካ ሙያ ያሉትን ለዚህ ሀገራዊ ጉዳይ እንዲያማክሩና በቀጠታም እንዲሳተፉ ማድረግ ጠቀሜታው ብዙ ነው። ለዚህ ሀገራዊ ጉዳይ የተጠየቁ ሁሉ ቀና ምላሽ እንደሚሰጡና በነፃም እንድሚያገለግሉ ጥርጥር የለንም። "እንዳያማህ ጥራው" ታልሆነ ነገሩ፤ ግብፅ በዚህ በዲፕሎማሲው በኩል ብዙ ጥላን እንደሄደች በግልጽ ይታያል። የኢትዮጵያ መንግሥትም ይህ የዲፕሎማሲ ጥረት የአንድ ሰሞን ግርግር ሳይሆን የግድቡ ጉዳይ ምዕራፍ እስኪያገኝ በቀጣይነት ማድረግ እንዳለበት ልናሳስብ እንወዳለን።

4) በምላሹ ምን ይገኛል

ከላይ እንደተጠቀሰው ግብጽ ኢትዮጵያችን ምንም ዓይነት የማልማት ሥራ እንዳታስብ፣ እንዳትጀምር፤ ከጀመረችም በዲፕሎማሲም፣ በገንዝብና ሌላ ተፅዕኖ አጣምራ ብጥብጥና ሁከት በማስደረግ ለማዳናቀፍ ትሠራለች። በተለይ የህዳሴው ግድብ ከተጀመረ ወዲህ የግብጽ ጣልቃ ገብነትና ተንኮል በከፍተኛ ማርሽ እየተንቀሳቀሰ ነው፤ በግልጽም የጦር ኀይል የመጠቀም ማስፈራሮም እያደረገች ነው። ብዙ ሰላዮችና የገንዘብ ወጪ በግድቡ አካባቢ አለመረጋጋትና የሰላም ማደፍረስ ተግባራትን ታስደርጋለች። ለአንድ አፍታም መዘንጋት የሌለበት ይህ ተንኮል፣ ጣልቃ ገብነትና ተፅዕኖ ግድቡ ተጠናቆ ሥራ ቢጀምርም የሚቆም አይደለም። "ያዳቆነ ሰይጣን . . ." እንዲሉ ኢትዮጵያችን አስፈላጊውን ራስ ጥበቃ በጦር ኀይልም፤ በደህንነትም እስካሁን እንደምታደርገው መቀጠል ይኖርባታል።

በቀጣይነት ኢትዮጵያችን ዐባይን በተመለከተ በምታደርገው የስምምነት ውል ሙሉ በሙሉ የሀገራችንን ጥቅም ከማስጠበቁም ባሻገር ግብጽ ጊዜ እየጠበቀች የምታደርገውን መተናኮልና በኢትዮጵያ ጉዳይ በየጊዜው ጣልቃ እየገባች ለአንዳንድ አማጽያን የፖለቲካ ድርጅቶች የምትሰጠውን ድጋፍና እርዳታ ማቆም እንዳለባት አስገዳጅ ውል ቢካተት መልካምነት ይኖረዋል።

ግብጽ አንድ ፍላጎቷ የህዳሴውን ግድብ በጣምራ ተቆጣጣሪነት የማስኬድ ፍላጎቷ በተዘዋዋሪ መንገድ ሀገርን በቅኝ ማስገባት ነውና ለስህተት እንዳንዳረግ እየተደረገ ያለው እምቢተኝነት መጠናከር

ይኖርበታል። በጦርነት ያገኘነውን የባድመ ድል በሰላም እንዳስረከብነው ዓይነት ስህተት በዐባይ እንዳይደገም ሕዝባችን የመንግሥትን አካሄድ በንቃት መጠባበቅ ይኖርበታል።

5) ሌላ አማራጮች - መስኖ በመስኖ

በሚደረገው ንግግር፤ አሁን እንዲሚስተዋለው ግብጽ ከአሜሪካ መንግሥት ኋላ ተደብቃ የኢትዮጵያችንን ብሔራዊ ጥቅም የሚጎዳ፣ ለእነርሱ ብቻ ያደላ ውል መፈረም እንዳለበት እየተናገረች ነው። ከላይ ከተጠቀሰው ኢትዮጵያችን ከድርድሩ በምላሹ ማግኘት ከምትፈልጋቸው የሰላምና የጣልቃ ገብነት መቆም ባሻገር ሌሎችንም አማራጮች ከባለሙያዎች በመመካከር ድርድሩ ውስጥም ውጪም መጥቀስ ያስፈልጋል። ግብጽ በጦር ኀይል የመጠቅምና ሌሎችንም አስፈላጊነታቸውን ያመንኩባቸው እርምጃዎች እውስዳለሁ ስትል ይሰማል። ኢትዮጵያችንም ነገሩ በዚህ ከቀጠለ፤ እኛም ግድቡ ከሚፈጥረው ሃይል ብቻ ሳይሆን ከራሱ ከዐባይም፤ ከገባር ወንዞቹም በመቶና ሺዎች የሚቆጠሩ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን መሥራት እንደምንችል ማሳሰብ ነው። የግድቡን ውሃ ከኀይል ማመንጨትና ዓሣ እርባታ ሌላ የመስኖ ልማት አለማቀዳችን ወደ ግብፅ የሚፈሰውን የውሃ መጠን ላለመቀነስ ባለን ዕምነት መሆኑን ግብጽን ሆነ የዓለም ሀገራትን ደጋግሞ ማሳሰብ ያስፈልጋል።

6) ካሣ ለተራዘመው አሞላል

ሌላው የድርድሩ መሰናክል ሆኖ በግብጽ በኩል የሚነሳው ጥያቄ ግድቡን በውሃ የመሙላቱ ጊዜ እስከ 20 ዓመት ድረስ መራዘም እንዳለበት ነው። ለዚህም በኢትዮጵያችን በኩል የምህንድስና፣ የኢኮኖሚና ፋይናንስ ባለሙያዎችን በማማከር በራሳችን የግብጽም የውሃ መጠኑ ሳይቀንስ በምን ያህል ጊዜ በመሙላት ኃይል ማመንጨት እንደሚችልና የልማት አስተዋጽዖውን ማስላት ያስፈልጋል። ይህ ከታወቀ ግብጽ ለምታቀርበው የማራዘም ጥያቄ፤ ኢትዮጵያችን የምታጣውን የገቢና የልማት ኪሣራ አስቦ ተገቢውን የገንዘብ ካሣ በምላሹ ማቅረብ ነው። ሙሌቱንም አራዝማ፤ የልማትም የገንዘብም ተጎጂ ሆና ግብጽን ብቻ ተጠቃሚ ማድረግ መናቅም፣ መሰደብም፣ ክብረነክም ነው።

7) ምርጫ 2012 ዝግጅት

መንግሥት በመጪው ነሐሴ 2012 ዓ.ም. ሊካሄድ የታሰበውን የምርጫ ዝግጅት በሦስት ምክንያቶች በማራዘም ወይም በማቆም ቅድሚያ ለዐባይ ብሔራዊ ጉዳይ መስጠት ይኖርበታል።

1. በአሁኑ ወቅት በዓለም ደረጃ የተከሰተውና እጅግ አሳሳቢ የሆነው የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ ጉዳይ ወዴት እንደሚያመራ ግልጽ ባይሆንም ለተለያዩ ስብሰባዎችም ሆነ ዝውውር አዳጋች መሆኑ ሊደረግ ለታሰበው ምርጫ እጅጉን እንቅፋት በመሆኑ፣
2. ሀገራችን በአሁኑ ወቅት ህልውናዋን የሚፈታተን አጣብቂኝ ሁኔታ ላይ በመገኘቷ መንግሥት የቅስቀሳ ሥራውን፣ ገንዘብና ጉልበቱን ሀገራዊ ጉዳይ ላይ በማድረግ ዐባይ የኢትዮጵያ ማንነት መሆኑን በማንኛውም መንገድ ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ታሪካዊ ወቅት ላይ ደርሰናልና ምርጫው ከሀገር በላይ አይደለምና ማራዘሙ አይጎዳም
3. ቀደም ሲልም እንዳስነበብነው አሁንም በሀገሪቱ ያለው ሰላምና መረጋጋት አስተማማኝ ባለመሆኑ እንደውም የዐባይ ጉዳይ የዘረኝነትን አባዜ ጠራርጎ በመበጣጠስ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን እያንከባለለ ያመጣልናልና ኢትዮጵያችን ያለ መንግሥት ይህን ወርቃማ አጋጣሚ ሊጠቀምበት ይገባል

ለማጠቃለል በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያችንና ዓለም ከፊታቸው የተደቀነ አሳሳቢ ወረርሽኝ እንዳለና እጅግ ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊደርስ የሚችለውን ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ቀውስ ለመቀነስ የሚደረገው መረባረብ ላይ የመንግሥት ጥረት እጅጉን ሊጠናከር ይገባዋል። ሕዝባችንም ለዚህ ዘግናኝ መቅሰፍት

ሳንረበሽና በአንዳንድ ስግብግቦች ሳንደናገጥ ማድረግ የሚገባንን ጥንቃቄ ትኩረት በመስጠት እንደየእምነታችን ልመናችንን ለፈጥሪ ማቅረብ ይኖርብናል።

ቤሌላ በኩል ዐባይን አስመልክቶ ግብጽ እየሸረበች ያለውን የኢትዮጵያን ሀገራዊ ሉዓላዊነትና አንድነት የመዳፈር አካሄድ ለመመከት የመዘጋጀት ብሔራዊ ግዴታ እንዳለብን መገንዘብ ይኖርብናል። ግብጽ በአሁኑ ወቅት የጦር መንደርደሪያ ሠፈር ለማግኘት በተለይ ከሻቢያ ጋር እየዶለተች ነውና በዚህ ጉዳይ ከግብጽ ጋር የሚተባበር ማንኛውም ሀገር ታሪካዊ ጠላታችን እንደሚሆን ማስገንዘብ የመንግሥት ኃላፊነት መሆኑን እንጠቁማለን።

እስከዛሬ እየተደረጉ ባሉ ድርድሮች ከግብጽ በኩል የሚሰጠን ትዕዛዝ መቆም ይኖርበታል። እንደውም ኢትዮጵያ በቀጣይነት የህዳሴውን ግድብ ሥራዋንና ዕቅዱን እየገፋችበት የተቋረጠውን ድርድር ለማስቀጠል ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ኃይሏን ማሳየት ይኖርባታል። እነዚህም ቅድመ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ ወደ ድርድሩ ለመምጣት፦

1. ዐባይ የኢትዮጵያችን መሆኑን ግብጽ መቀበል ይኖርባታል።
2. ግብጽ በቅድሚያ ኢትዮጵያ በዐባይ ላይ የመጠቀም ሙሉ መብት እንዳላት ማወቅ ይኖርባታል።
3. ግብጽ የጀመረችውን ወታደራዊ ዛቻ ሙሉ በሙሉ ማቆምና ከኢትዮጵያ አጎራባች ሀገራት መንደርደሪያ ይሆናት ዘንድ የጦር ሠፈር ለማግኘት የምታደርገውን ጥረት ስታቆም
4. የህዳሴውን ግድብ ሥራ ለማጠናቀቅ ለተለያዩ ዕቃ አቅራቢ ኩባንያዎችና ድርጅቶች አቅርቦታቸውን እንዲያቋርጡ ግብጽ የምታደርገውን ዘመቻ ሙሉ በሙሉ ስታቆም
5. በማንኛውም የኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳይ የምታደርገው ጣልቃ ገብነት ሙሉ በሙሉ ስታቆም

ኢትዮጵያ ወደ ቀጣይ ድርድር እንደምትመጣ ማሳወቅ ይጠበቅባታል።

ኃይላችን ሕዝባችን፣ ክብራችን ሀገራችን፣ ዐባይ ኢትዮጵያችን ነውና ለዚህ ደግሞ ሀገራዊ አንድነታችንን አጠናክረን ለአንዴም ለሁሌም የዐባይን ጉዳይ እልባት መስጠት ያለብን እኛው ኢትዮጵያውያኖች መሆናችንን የምናስመሰክርበት ወቅት መሆኑን "***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" አበክረን እንጠቁማለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!!!
የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ ከዓለማችን ይርቅልን ዘንድ ፈጣሪ ይርዳን!!!
አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ
መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም. (March 23, 2020)

ማሳሰቢያ ፡

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጬት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin